አንቀጽ ፪ የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 15

አንቀጽ ፫ የሰበካ ጉባኤው ዋና ጸሐፊ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 16

አንቀጽ ፭ የስብከተ ወንጌልና የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ተወካይ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 17

አንቀጽ ፮ የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ተወካይ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 18

አንቀጽ ፯ የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) እና ጤና አገልግሎት ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 19

አንቀጽ ፰ የዕቃ ግዢ እና የሕንፃ ጥገና ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 19

አንቀጽ ፱ የሒሳብ ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 20

አንቀጽ ፲ የገንዘብ ቤት እና ንብረት አስተዳደር ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 21

አንቀጽ ፲፩ የእቅድና ልማት ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 22

አንቀጽ ፲፪ የአባላት ግንኙነት እና የሚድያ ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 22

**ምዕራፍ ፬ - ልዩ ልዩ ክፍሎች 24**

አንቀጽ ፩ የቁጥጥር እና ክትትል ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 24

አንቀጽ ፪ የካህናት ጉባኤ ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 25

አንቀጽ ፫ የጽሕፈት ቤት አስተዳደር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት 26

**ምዕራፍ ፭- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 27**

አንቀጽ ፩ አባልነት 27

አንቀጽ ፪ የቤተ ክርስቲያኗ ጠቅላላ ጉባኤ 31

አንቀጽ ፫ ቤተ ክርስቲያኗ ከሀገረ ስብከቱ ጋር ያላትን ግንኙነት በተመለከተ 32

አንቀጽ ፬ ቤተ ክርስቲያኗ የተቋቋመችበት ቀን 32

አንቀጽ ፭ የበጀት ዓመት እና የምርጫ ወቅት 32

አንቀጽ ፮ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ 32

አንቀጽ ፯ አጥቢያችን እንደ ቤተ ክርስቲያን መቀጠል ባትችል 33

DRAFT

፯ ከቤተ ክርስቲያኗ የውስጠ ደንብ ዋና ሐሳብ ሳይወጣ ለክፍሉ አገልግሎት የሚረዳ የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፤ በሰበካ ጉባኤው ሲጸድቅም በአገልግሎት ላይ ያውላል።

## አንቀጽ ፯

## የዕቃ ግዢ እና የንብረት ክፍል ~~የሕንፃ ጥገና ክፍል~~ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

~~የዚህ ክፍል ዋና ተግባሩ ዕለት ከዕለት ለቤተ ክርስቲያኗ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግዢዎችን መፈጸም ሲሆን፣ በተጨማሪም የሕንፃ ግዢ እና ዕድሳት ንዑስ ክፍልን ያቋቁማል፤ በኃላፊነትም ይመራል።~~

፩ <u>የዕቃ ግዢ ክፍል ንዑስ ክፍል</u>

- ሀ) ዕለት ከዕለት ለቤተ ክርስቲያኗ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግዢዎችን ይፈጽማል፤
- ለ) በቤተ ክርስቲያን ያለውን ቋሚ ንብረት ይቆጣጠራል። ~~መፈጸም ሲሆን፣ በተጨማሪም የሕንፃ ግዢ እና ዕድሳት ንዑስ ክፍልን ያቋቁማል፤ በኃላፊነትም ይመራል።~~
- ሐ) ለቤተ ክርስቲያኗ የውስጥና የውጭ አገልግሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳትንና ሌሎችንም ቁሳቁሶች በሚዘጋጀው ማዘዣ መሠረት ገዝቶ ያቀርባል፤
- ~~መ) ለበዓላት መስተንግዶ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስና የምግብ ማዘጋጃ ገንዘብ ከሒሳብ ክፍል ቀደም ብሎ በማውጣት ለሚፈለገው አገልግሎት ያውላል፤~~
- ሠ) የግዢ ደረሰኞች በተገቢው ሁኔታ ተይዘው ለሒሳብ ክፍል ገቢ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ረ) የቤተ ክርስቲያኗን የተለያዩ ክሬዲት ካርዶች በአግባቡ ለታዘዘው አገልግሎት ያውላል፣ በኃላፊነትም ይይዛቸዋል፤
- ሰ) በሥሩ ንዑሳን ክፍሎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያዋቅራል፤
- ሸ) ከቤተ ክርስቲያኗ የውስጠ ደንብ ዋና ሐሳብ ሳይወጣ ለክፍሉ አገልግሎት የሚረዳ የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፤ በሰበካ ጉባኤው ሲጸድቅም በአገልግሎት ላይ ያውላል።

፪ <u>የንብረት አስተዳደር ንዑስ ክፍል</u>

- ሀ ከቁሰ ገበዙ ወይም ከአስተዳዳሪው ታቦተ ሕጉን ጨምሮ የቤተ መቅደስ ንዋያተ ቅድሳት ብዛታቸውና ዓይነታቸው ተመዝግቦ ሲመጣ በልዩ መዝገብ ይይዛል፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ ንብረቶች በሚገባ በመዝገብና በኮምፒውተር ተመዝግበው እንዲያዙ ያደርጋል፤
- ለ ቋሚውን ንብረት ከአላቂው በመለየት መዝግቦ ይይዛል፤
- ሐ ለቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ መገልገያዎችን ሁሉ ከካህናት ጋር በመነጋገር እንዲሟሉ ያደርጋል፤
- መ በየዓመቱ መጨረሻ የቤተ ክርስቲያኗን አጠቃላይ ንብረት ቆጠራ ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለሰበካ ጉባኤው ያሳውቃል።
- ሠ ከቤተ ክርስቲያኗ የውስጠ ደንብ ዋና ሐሳብ ሳይወጣ ለክፍሉ አገልግሎት የሚረዳ የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፤ በሰበካ ጉባኤው ሲጸድቅም በአገልግሎት ላይ ያውላል።

DRAFT

